# በሃገር ሞት መነገድ!

### ከዓሣዩ

*የወተት እፍታው በእሣት እሥኪመታ*
*ዓበው እንዳሉቱ ትላንት በጨዋታ፤*
*በኣራቱም ማዕዘናት ውጊያው ሲበረታ*
*ሠልፍ ቁሞ የነበረው፤ ከታጋይ ጎን ተርታ*
*ትግሉን ኣዘናግቶ በጠላት ሊያሥመታ፤*

**ዛሬ ደግሞ!**

*የደደቢቱ  ዛር ሞለከሥኩኝ ብሎ*
*ዳግም ሊበትንህ ከነ እንቶኔ ሁኖ፤*
*ሊመታህ ነውና ታጋይ ሣትሰጥ ፋታ*
*ጨክነህ ተዋጋው ትጥቅህን ሣትፈታ*
*በሃገር ሞት ነጋጆች ፍጹም ሣትረታ !።*

*ጮማ እየቆረጡ፤ ውሥኪ እየተራጩ*
*ከመለስ በረከት ጽዋን እያጋጩ፤*
*በትግል መሞትን ፈጽሞ የማያውቁ*
*በሸራተን ኣዋጅ ለሥልጣን ሊበቁ፤*
*የሕዝብ ነፃነቱን፤ መብቱን ሊያሣንቁ*
***ሊሾሙ በሃገር ሞት፤ በፊርማ ኣጸደቁ ።***

***ሥለዚህ!***

*በሕዝቡ ሰቆቃ በረሃብተኛው ጠኔ*
*በህፃናት ሽያጭ ሲከብር ወያኔ፤*
*ደግሞም ተወድሦ ኮሾ ተቃዋሚ*
***ለሃገር ሟች ሲወገዝ፤ ቃልኪዳን ኣክባሪ፤***
*ስንዴን ከእንክርዳዱ፤ በደንብ ኣበጥሮ*
*እያንገዋለለ በአመጽ ኣሽቀንጥሮ*
*ኣሁንሥ ኣይቀርም፤ ቁርጥ ነው ዘንድሮ፤*
*ባፍጢሙ ሲደፋው፤ የታሪክ ግብር ከፍሎ*
***በሃገር ሞት መነገድ፤ከእንግዲህ ይብቃ ብሎ!።***

12/10/09

This document was created with Win2PDF available at http://www.win2pdf.com.
The unregistered version of Win2PDF is for evaluation or non-commercial use only.
This page will not be added after purchasing Win2PDF.